# ምድብ አንድ (የሙዓለ ሕፃናት ተማሪዎች)
## 25 ኛ ሳምንት
## ዳዊትና ዮናታን

**ዓላማ**

- ስለ እውነተኛ ወዳጅነት መማር።

**ምንባብ**

- 1ኛ ሳሙ.18-20 እና 2ኛ ሳሙ.1 እና 9

**መግቢያ**

ባለፈው ሳምት ዳዊት ግዙፉን ጎልያድ በእግዚአብሔር ኃይል ካሸነፈ በኋላ እስራኤላውያን ***"ሳኦል ሺ፣ ዳዊት አሥር ሺ ገደለ።"*** እያሉ ማመስገናቸውን ታስታውሳላችሁ?...አዎን ዛሬ ሳኦል በቅንዓት ዳዊት ላይ እንደተነሳበት እንማራለን። በተጨማሪም በሳኦል ልጅ በዮናታንና በዳዊት መሐል የነበረውን ፍጹም ወንድማማችነትም እናያለን።

**ትምህርቱ**

***ዮናታን ለዳዊት***

- የመጀመሪው የእስራኤል ንጉሥ ሳኦል ዮናታን የተባለ ልጅ ነበረው።
- ዳዊት ግዙፉን ጎልያድን ከገደለው በኋላ ዮናታን እጅግ ዳዊትን ወዶት፤የራሱን ልብስና ሰይፍም ሸልሞታል፤፤
- ዳዊት ከንጉሥ ከሳኦል በላይ በእስራኤላውያን ዘንድ ታዋቂ ሆነ።ንጉሱ ሳኦልም በዚህ ቀንቶ ዳዊትን ለመግደል ፈለገ።
- አንድ ቀን ሳኦል ታምሞ ዳዊት በገና እየደረደረለት፤ጦር ወረወረበት፤ዳዊትም ዘወር ብሎ አመለጠ።
- ከዚያም በተደጋጋሚ ሊገድለው እንደሚፈለግ አውቆ ዳዊት ሸሸ።በሌላ ሥፍራም ሄዶ ተቀመጠ፤እስራኤላውያን ግን ዳዊትን ይወዱት ነበር።
- አንድ ቀንም የሳኦል ልጅ፣የዳዊት ወዳጅ ዮናታን አባቱን ***"እርሱ አለበደለህምና ሥራውም ለአንተ እጅግ መልካም ሆኖአልና ንጉሡ ባሪያውን ዳዊትን አይበድለው"*** ብሎ ተናገረው።
- ንጉሡም በልጁ ንግግር ተደሥቶ ለጊዜው ዳዊትን እንደማይገድለው ቃል ገባለት።ነገር ግን ቅናቱ ተነስቶበት በድጋሚ ሊገድለው ፈለገ።ዮናታንም ሳኦልን አስመለጠው።
- ስለዚህም በሳኦል ልጁ ዮናታንን ***"ዳዊት በሕይወት ካለ አንተ ንጉሥ አትሆንም"*** አለው።
- ዮናታን ግን ንጉሥ ለመሆን ከመጓጓት ይልቅ ለወዳጁ ለዳዊት ተጠነቀቀለት።ምልክት ሰጥቶም አስመለጠው።(መምህር በዳዊትናበዮናታን መካል የነበረውን ምልክት ያስረዱ።) 1ኛ ሳሙ. 20÷18-42
- ዮናታንናዳዊት በምሥጢር ተገናኙተው፣ተቃቅፈውና ተለቃቅሰውም ተለያዩ፤ለምን ያለቅሱ ይመስላችኋል? አዎን የሚዋደዱ ጓደኞች ስለነበሩ ነው፤
- ዮናታንና ዳዊትን ***"በደኅና ሂድ፤ እነሆ÷ በእኔና በአንተ መካከል ለዘለዓም እግዚአብሔር ይሁን"*** አለ። ዳዊት ተሰደደ ዮናታንም ወደ ከተማ ገባ።

***ዳዊት ለዮናታን***

- ዮናታን ***ቸርነትን እንዳደረግሁልህ ለኔም ቸርነትን አድርግልኝ*** ባለው መሰረትና እግዚአብሔርን መሐላቸው እንዳደጉ ዳዊትም የዮናታንን መልካምነት አሰበ።
- ዳዊት ከሳኦል ቤተመንግሥት ከሸሸ በኋላ ፍልስጤማውን እስራኤልን ተዋጉ።ሳኦልና ሦስት ልጆቹ የዳዊት ወዳጅ ዮናታንን ጨምሮ ሞቱ።
- ዳዊትም በስደት ሆኖ ይሄን ሲሠማ በጣም አዘነም አለቀሰም።
- ከዚህ በኋላም ዳዊት የእስራኤል ንጉሥ ሆነ።በርሱና በዮናታን መካከል የነበረውን እግዚአብሔርንና የዮናታንን ቅናነት አሰቦም፤ለዮናታን ቤተሰቦች መልካም ለማድረግ ወሰነ።ሲያጠያይቅም የዮናታን ልጅ መኖሩን አረጋግጦ አስጠራው።ልጁም ለንጉሡ የሚገባውን ክብር ሰጥቶ ወደ ዳዊት መጣ።
- ንጉሡ ዳዊትም ***"ስለ ዮናታን መልካም አደረግልሃለሁ÷የሳኦልን መሬት በሙሉም ውሰድ"*** አለው።በጦርነቱ ወቅት አሳዳጊው ይዛው ስትሸሽ ውድቆ የተጎዳው ልጅም ንጉሡን አመስግኖ በደስታ ሄደ።
- ዳዊት ለዮናታን የነበረውን ፍቅርና ውለታውን ለልጁ መልካም በማድረግ አሳየ።

**ጥያቄዎች**

1.ሳኦል ዳዊትን ለመግደል ለምን ፈለገ?
2. የሳኦል ልጅ የዳዊት ወዳጅ ማን ነበር?
3. ቅናት ምንድን ነው?
4.በዳዊትና በዮናታን መካከል የነበረው ቃል ኪዳን ምን ነበር?
5. ዳዊት ቃሉን ጠብቋል? እንዴት?
6. ሳኦልና ዮናታን ሲሞቱ ዳዊት ምን ተሰማው?
7. ዮናታን እውነተኛ ወዳጅ ነበር? ለምን?

***መዝሙር፡-***

እግዚአብሔር ይወዳናል ይጠብቀናል(2)
እርሱ ለኛ ደሙን ክሶልናል(2)

# Friends



*"A friend loves at all times."* ( Proverb 17:17)

ይቆየን::